# ለኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች የ2012 ዓ.ም መግቢያ ፈተና የምዝገባ ጥሪ

በአገራችን እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠልና የአገሪቱን በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎት ለማሟላት በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ከፍተኛ የለውጥ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። ይህንንም እውን ለማድረግ ልዩ ተልዕኮ ተሰጥቷቸው የተደራጁትን የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥራት ማዕከላት በማድረግ በዘርፉ ብቃት ያላቸውን ሙያተኞችን እያፈሩ ይገኛሉ።

በመሆኑም በ2012 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በአፕላይድ ሳይንስና በኢንጂነሪንግ ዘርፎች ትምህርታቸውን መከታተል ለሚፈልጉ በ 2011 ዓ.ም. የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የወሰዱና ከታች የተጠቀሱትን ዝርዝር መስፈርቶች የሚያሟሉ ተማሪዎችን ተጨማሪ የመግቢያ ፈተና በቀጥታ (online) በመስጠት መቀበል ይፈልጋሉ።

**የመመዝገቢያ መስፈርቶች፡-**

| ትምህርት መስኮች | ውጤት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ለታዳጊ ክልሎች (አፋር፤ሱማሌ፤ቤ.ጉሙዝ፤ ጋምቤላ) | | ለሌሎች ክልሎች | |
| | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| ኢንጂነሪንግ | ከ420 በላይ | ከ410 በላይ | ከ430 በላይ | ከ420 በላይ |
| አፕላይድ ሳይንስ | ከ360 በላይ | ከ350 በላይ | ከ380 በላይ | ከ360 በላይ |

**የትምህርት መስኮች:-**

| አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ | | አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ | |
|---|---|---|---|
| **ኢንጂነሪንግ** | **አፕላይድ ሳይንስ** | **ኢንጂነሪንግ** | **አፕላይድ ሳይንስ** |
| አርክቴክቸር | ባዮቴክኖሎጂ | አርክቴክቸር | አፕላይድ ባዮሎጂ |
| ሲቪል ኢንጂነሪንግ | ኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ | ሲቪል ኢንጂነሪንግ | አፕላይድ ኬሚስትሪ |
| ኬሚካል ኢንጂነሪንግ | ፉድ ሳይንስና አፕላይድ ኒዩትሪሽን | ኬሚካል ኢንጂነሪንግ | አፕላይድ ፊዚክስ |
| ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ | ጂኦሎጂ | ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ | አፕላይድ ጂኦሎጂ |
| ኤሌክትሪካል እና ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ | | ኤሌክትሮኒክስ ፓወር እና ኮንትሮል ኢንጂነሪንግ | አፕላይድ ማቲማቲክስ |
| ኤሌክትሮሜካኒካል ኢንጂነሪንግ | | ኤሌክትሮኒክስ እና ኮሚኒኬሽን ኢንጂነሪንግ | |
| ሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ | | ኮምፒዩተር ሳይንስና ኢንጂነሪንግ | |
| ኢንቫይሮሜንታል ኢንጂነሪንግ | | ወተር ሪሶርስ ኢንጂነሪንግ | |
| ማይኒንግ ኢንጂነሪንግ | | ማቴሪያል ሳይንስና ኢንጂነሪንግ | |

**የምዝገባ ጊዜ:-**

- **ከነሐሴ 13 እስከ 22 ቀን 2011 ዓ.ም.**

**ምዝገባው የሚጠናቀቀው:-**

- ነሐሴ 22 ከሌሊቱ 6:00 ሰዓት ይሆናል፡፡

**የምዝገባ ቦታ:**

- የምዝገባ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾች በማንኛውም ስፍራ በኢንተርኔት (online) በ www.aastu.edu.et
  www.astu.edu.et ድህረ ገፅ በመጠቀም መመዝገብ ይችላሉ፡፡

**ፈተናው የሚሰጥበት ቀን:-**

- በማስታወቂያ እና በዩኒቨርሲቲዎቹ ዌብሳይት የሚገለጽ ይሆናል፡፡

**ፈተናው የሚሰጥበት ቦታ:-**

- በምዝገባ ወቅት በመረጡት የፈተና ጣቢያ በአካል በመቅረብ ይሆናል፡፡

**ማሳሰቢያ:-**

1) ለምዝገባና ለፈተና ምንም አይነት ክፍያ አይጠየቅም፣

2) ከሚመዘገቡት አመልካቾች ውስጥ ለፈተና የሚቀርቡት ስም ዝርዝራቸው በሚከተሉት ድረ-ገፆች፡-

www.aastu.edu.et, www.astu.edu.et

እንደአመቺነቱም በስልክ አጭር የጽሑፍ መልዕክት የሚገለፅ ይሆናል፡፡

3) አመልካቾች ከወዲሁ ፈተናው በሚሰጥባቸው የትምህርት ዓይነቶች፣ ማለትም የመሰናዶ (11ኛ እና 12ኛ ክፍል) ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ሂሳብና እንግሊዝኛ እንዲዘጋጁ ይመከራል፡፡

4) ፈተና የሚሰጠው በቀጥታ (online) ስለሆነ አመልካቾች በፈተና ጊዜ ሊያጋጥም የሚችል ግራ መጋባትን ለማስቀረት በምዝገባ ጊዜ ከመመዝገቢያ ፎርማቱ ጋር ተያይዞ የቀረበውን የሙከራ ፈተና እንዲለማመዱ ይመከራል፡፡

5) አመልካቾች ለፈተና ሲቀርቡ የ2011 ዓ/ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት፣ የሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና አድሚሽን ካርድ (ወይም መታወቂያ) እና የምዝገባ ማረጋገጫ ኮፒ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6) የመግቢያ ፈተናውን የሚያልፉ አመልካቾች በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚደረገው የዩኒቨርሲቲ ምደባ ውስጥ አይካተቱም፡፡

7) በውጤታቸው የተመረጡ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ምደባ ከላይ በተጠቀሱት ድህረ-ገፆች ይገለፃል፡፡

8) በመስፈርቱ መሰረት ያልተመረጡ አመልካቾች ከዚህ በፊት እንደሚደረገው በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በኩል በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ ይሆናል፡፡

9) በፈተናው ዕለት ማንኛውንም የሞባይል ስልኮችን ይዞ ወደ ፈተና ጣቢያ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

10) በፈተና ወቅት ያልተገባ ተግባር መፈፀም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

ለተጨማሪ ማብራሪያ ከላይ የተጠቀሱትን ድረ-ገፆች መጎብኘት ይቻላል፡፡

## የአዲስ አበባ እና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች